እትም 1
ቁጥር 1

2013

ሰብአዊነት

የስብስብ ለሰብአዊ መብቶች በኢትዮጵያ መፅሄት



ገለልተኛ አጣሪ ጉባኤ ከመተከል እስከ መቀሌ
ኖህ የሱፍ|ገፅ ፩

CONFLICT AND SEXUAL VIOLENCE: HIGHLIGHTING THE CASE OF ETHIOPIA
Mahlet Abreham | p. ፬

የንፁሀን ዜጎች ጥበቃ በጦርነት ወቅት
ማህሌት ንጉሴ | ገፅ ፯

አዘጋጆች

ዋና አዘጋጅ

ቃልኪዳን ተስፋዬ

ከቅድስት ማርያም ዩኒቨርሲቲ በ**computer science** የመጀመሪያ ዲግሪ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በእግሊዝኛ ቋንቋ እና ስነ- ጽሁፍ ማስተርስ ዲግሪ

ፀሀፊ፣ ገጣሚ እና የሴቶች መብት ተሟጋች

Email- Kalkidanzewdie4@gmail.com

የህትመት ዲዛይነር

ቤርሳቤህ ሰለሞን

ከድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሰብአዊ መብቶች ህግ ሁለተኛ ዲግሪ

Email- solomonbersabeh19@gmail.com

አርታኢ

ኖህ የሱፍ

ከወሎ ዩኒቨርስቲ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሰብአዊ መብቶች ህግ ሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ

Email- noahyesufyimer@gmail.com

የህትመት አስተባባሪ

ማህሌት ንጉሴ

ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ እና የሰብአዊ መብቶች ተሟጋች

Email-mahletnegussie12@gmail.com

Get in touch with us!

our official website at https://ahrethio.org

+251 910921294 edenjossy@gmail.com

t.me/joinchat/VEOpcdtoSCUxFUUN

ርዕሰ አንቀጽ

ከሁለት አመት በፊት የተጀመረው የፖለቲካ ለውጥ በሀገራችን ውስጥ ያለውን አስከፊ የሆነ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በማሻሻል ረገድ ጥሩ ተስፋ የተጣለበት ነበር ። በተለይም ለውጡን እየመራ ያለው ሀይል ወደ ስልጣን ከመጣበት ጊዜ አንስቶ በርካታ የፖለቲካ እስረኞችን መልቀቁ፣ በሰብአዊ መብቶች ላይ ከፍተኛ ገደብ እና ጫና ያሳድሩ የነበሩ አፋኝ የሕግ ማዕቀፎች እንዲሻሻሉ ማድረጉ፣ ሃሳብን የመግለጽ እና የመናገር መብትን ጨምሮ ሌሎች መሰረታዊ መብቶች እና ነጻነቶች እንዲከበሩ የፖለቲካ ምህዳሩን ማስፋቱ፣ የሲቪክ ማህበራት ላይ ተጥሎ የነበረው የመደራጀት መብትን የሚገፈው ጫና እንዲነሳ ተደርጎ የሲቪክ ምህዳሩም እንዲሰፋ መደረጉ፣ ከአገር ውጭ በስደት የቆዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ሃገር ቤት እንዲመለሱ መደረጉ እና ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ወሳኝ የሆኑ ተቋማት በአዲስ መልክ እንዲዋቀሩ እና ገለልተኛ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ መደረጉ የብዙዎችን ተስፋ ከፍ አድርጎት ነበር።

ይሁን እንጂ የለውጥ ጉዞው ብዙም ፈቅ ሳይል በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የእርስ በእርስ ግጭቶች፣ ብሔርን እና ማንነትን ኢላማ ያደረጉ የጥቃት እርምጃዎች በማያባራ መልኩ መከሰት ጀመሩ። አንዳንዶቹ ክስተቶችም ለብዙ ሰዎች መገደል፣ ከፍተኛ ግምት ላለው የሕዝብ እና የመንግስት ንብረት መውደም ምክንያት ሆነዋል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችም ቤት፣ ንብረታቸውን ጥለው ለመሰደድ እና ከኖሩበት ቀዬ ለመፈናቀል በቁ። ይህም ሁኔታ የአገሪቱን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ እጅግ እንዲያቆለቁል እና አስፈሪ ወደ ሆነ ደረጃም እንዲደርስ አድርጎታል። በተለይም በቅርቡ በትግራይ ክልል የተከሰተው ጦርነት ለመቶ ሺዎች መፈናቀል እና ቁጥሩ እስካሁን በውል ላልታወቀ የሰው ህይወት መጥፋት ምክንያት ሆኗል። ጦርነቱ ያስከተለው ሰብአዊ ቀውስም የአገሪቱን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ እጅግ የከፋ ደረጃ ላይ አድርሶታል።

ከላይ የተገለጹት ግጭቶች ባስከተሉት የፖለቲካ ውጥረት እና በየክልሉ በተከሰቱ ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ውስጥ ያለችው አገራችን በብዙዎች ዘንድ ከፍተኛ ግምት የተሰጠውን 6ኛውን ብሔራዊ ምርጫ ለማካሄድ ከአንድ ወር ብዙም ያልገፋ ጊዜ ይቀራታል። ምርጫውን ተከትሎ የሚታየው የፖለቲካ ውጥረትም የአገሪቱን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ወደ አሳሳቢ ደረጃ እያደረሰው ይገኛል።

ይህ ምርጫ ነጻ፣ ፍትሐዊ እና ሰላማዊ በሆነ ሂደት መጠናቀቁ ለአገራችን ትልቅ እና ወሳኝ ምዕራፍ እንደሆነ ድርጅታችን በጽኑ ያምናል። ምርጫ ለአንድ ማህበረሰብ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመዘርጋት ከሚያስችሉ ወሳኝ ክንውኖች መካከል አንዱና ዋናው ነው። በመሆኑም ይህ ምርጫ ዜጎች የሥልጣን ባለቤት መሆናቸው የሚረጋገጥበት እና በኢትዮጵያ ታሪክም ውስጥ በምርጫ ካርድ መንግስት የሚዋቀርበት አዲስ ምዕራፍ ስለሚሆን ሂደቱ እና ፍጻሜው የተቃና እንዲሆን ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩሉን ኃላፊነት ሊወጡ ይገባል። መንግስት ምርጫው በሰላም እንዲጠናቀቅ ከማንም በላይ ኃላፊነት አለበት። ምርጫው ነጻና ፍትሐዊ እንዲሆንም በአዲስ መልክ የተዋቀረው የምርጫ ቦርድ በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ቢሆንም በብዙ መልኩ ሊደገፍ ይገባዋል። ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችም አማራጭ ሃሳባቸውን ይዘው የነቃ ተሳትፎ በማድረግም ሆነ ራሳቸውን ከአመጽ እና ከሕገ-ወጥ ተግባራት በማቀብ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል። የሲቪክ ማህበራት፣ የኃይማኖት ተቋማት እና የሙያ ማህበራትም ዜጎችን በማንቃት፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ ቅራኔዎችን በማጥበብ እና መልካም ዜጋ በመፍጠር ትልቅ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል። ምርጫው የተሳካ እና ሰላማዊ እንዲሆን ስብስብ ለሰብአዊ መብቶች በኢትዮጵያ ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ጥሪውን ያቀርባል።

ገለልተኛ አጣሪ ጉባኤ: ከመተከል እስከ መቀሌ

ኖህ የሱፍ(፩)

መቅድም

ባለፉት ጥቂት አመታት ኢትዮጵያ ውስጥ እየታየ ያለው ማንነት ላይ ያተኮረ ተደጋጋሚ ጥቃት እጅግ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል። ድርጅታችን፤ ስብስብ ለሰብአዊ መብቶች በኢትዮጵያ በማንነት ላይ ያነጣጠሩትን ጥቃቶች በማስመልከት ተደጋጋሚ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ያወጣ ሲሆን ለመንግስት እና ለሚመለከታቸው አካላትም ጥብቅ ምክር አዘል ማሳሰቢያዎችንና የመፍትሔ ሃሳቦችንም ሲያቀርብ ቆይቷል። ይሁንና እነዚህ የጥቃት አይነቶች በቂ የሆነ ትኩረት ከመንግስት እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ስላልተቸራቸው ተደጋግመው ሊከሰቱ ችለዋል። ቁጥሩ ቀላል የማይባል የሰው ህይወት በአሰቃቂ ሁኔታ ሲጠፋ ፤ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው የሕዝብ እና የመንግስት ንብረትም ወድሟል፤ በተጨማሪም በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎችም ተፈናቅለዋል።

በዚህ ጉዳይ ላይ የመብት ተሟጋች ድርጅቶች ገለልተኛ በሆነ አካል ምርመራ እንዲካሄድባቸው እና በአጥፊዎቹም ላይ አፋጣኝ የሆነ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ሲወተውቱ ቆይተዋል። ይሁንና ለዚህ ጥያቄ ቀና እና አፋጣኝ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ አንዳንድ የመንግስት ባለስልጣናትም ሆነ ግለሰቦች እራሳቸውን ከተጠያቂነት ለማሸሽ በማሰብ ጥያቄዎችን ሲሸሹ እና አልፎ አልፎም ጥያቄውን ባነሱት አካላት ላይ ያነጣጠረ ነቀፌታ እና ቅስቀሳ ሲያደርጉ ደጋግሞ ይስተዋላል። ለምን ይሆን? በሕግ የተጣለባቸውን ኃላፊነት ካለማወቅ? ወይስ የጥፋቱ ተባባሪ በመሆን? ወይስ ለጉዳዩ ትኩረት ካለመስጠት? በዚህ የዳሰሳ ጽሁፍ በኢትዮጵያ ገለልተኛ አጣሪ ጉባኤ ከማቋቋም ጋር በተያያዘ የሚታዩ ብዥታዎችን ለማጥራት እሞክራለሁ። ይህ ፅሁፍ በርዕሰ አንቀፅ ከመተከል እስከ መቀሌ በሚል ይገለፅ እንጂ ከመተከል በመለስ ያሉትንም የመብት ጥሰቶች ለመዳሰስ ይሞክራል።

"ገለልተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት አጣሪ ጉባኤ ማለት በአንድ አገር ወይም ሥፍራ በመንግስት አካላት ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት የተፈጸመን ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት እንዲያጣራ በሕግ ወይም በመንግስት በጎ ፈቃድ የሚቋቋም ገለልተኛ የሆነ የባለሙያዎች ቡድን ነው። አጣሪው ጉባኤ ገለልተኛ ፣ ነፃ እና ብቁ መሆን ይኖርበታል።"

መግቢያ

ገለልተኛ የሰብአዊ መብቶች አጣሪ ጉባኤን ማቋቋም ታሪካዊ ዳራውን ስንመለከተው ለመጀመሪያ ጊዜ በ19ኛው ምዕተ አለም በእንግሊዝ ተግባራዊ መደረግ የጀመረ መሆኑን ሰነዶች ያመላክታሉ።(2) ይህን ተከትሎም በ20ኛው ምዕተ አለም ከእንግሊዝ ውጭ በተለያዩ አገራት ሲተገበር ቆይቷል። ገለልተኛ አጣሪ ጉባኤ የሚያስፈልጋቸው የሰብአዊ መብት ጥሰቶችነ በአይነታቸው ለየት ያሉ ሲሆኑ የጥሰቱ አይነት እና ባህሪ መጠና ሰፊ እና ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ያስከተለ ሲሆን እና በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ለጥሰቱ ምክንያት የሆኑት ጉዳዮች ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸውን ወይም የተለያዩ የፖለቲካ አካላት ለጥሰቱ ምክንያት ናቸው ተብሎ በሚገመትባቸው ጉዳዮች ላይ ገለልተኛ የሆነ አጣሪ የምርመራ አካል እንዲሰየም ሊጠየቅ ይችላል።

እንዲህ አይነት ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሲከሰቱ አፋጣኝ እና ተገቢ ምላሽ እንዲሰጣቸው፣ የተፈፀሙትን ጥሰቶች በጥልቀት ለማጣራት እና ለጥሰቱ ተጠያቂ መሆን የሚገባቸው አካላት ተለይተው እንዲታወቁና ተጠያቂ እንዲሆኑ ለማድረግ ከማንኛውም ወገንተኝነት ነጻ የሆነ ፤ ሙያዊ ብቃት እና በቂ ልምድ ያላቸው ሰዎች የሚሳተፉበትና፣ የተለያዩ ተቋማትን ያሳተፈ አጣሪ ጉባኤ እንድቋቋም ይደረጋል።

1. ጸሀፊው ከውሎ ዮኒቨርስቲ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ አለው።በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሰብአዊ መብቶች ህግ የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ ነው።

2. Philip Alston, 'Introduction: Commissions of Inquiry as Human Rights Fact-Finding Tools' American Society of International Law 105 (2011) 81.

ብዙውን ጊዜ በተለይም ገለልተኛ የፍትሕ ተቋማት በሌሉበት እና የከፋ የመብት ጥሰት በሚፈጸምበት አገር ውስጥ መንግስታት እንዲህ ያለ ገለልተኛ አካል እንዲቋቋም እና የማጣራት ሥራ እንዲያከናውን አይፈቅዱም። በመሆኑም በእንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ በሚገኙ አገራት የተፈጸሙ አስከፊ የመብት ጥሰቶችን የሚያጣራ ገለልተኛ አካል ሊቋቋም የሚችለው በሲቪል እና በአለም አቀፍ ማህበረሰቡ ጥብቅ ውትወታ እና ጫና ነው።

የገለልተኛ አጣሪ ጉባኤዎች አስፈላጊነት እና አንግበው የሚነሱት አላማ ተፈጽመዋል የሚባሉ ወይም የተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በቦታው በመገኘት ማጣራት፤ ለተፈፀሙ ጥሰቶች የመንግስትን ብሎም የግለሰቦችን ሃላፊነት መወሰን ፤ ሊደረጉ በሚገባቸው እንደ ካሳ (reparation) እና ማሻሻያ (reform) እና ሌሎች ጉዳዩች ላይ የመፍትሄ ሀሳቦችን ለመስጠት ነው።(3) በተጨማሪም እነዚህ ተቋማት ቀጣይ ለሚደረጉ የክስ ሂደቶች እና የወንጀል ተጠያቂነትን ለመመስረት እንደ መነሻ በማገልገል ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። የገለልተኛ አጣሪ ጉባዔው አመሰራረትም ሆነ ሥራዎቹን የሚያከናውንባቸው መንገዶች አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት መርሆዎችን እና የአሰራር ስልቶችን የተከተለ መሆን እንዳለበት ይታመናል።

ገለልተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት አጣሪ ጉባዔ ምን ማለት ነው?

ገለልተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት አጣሪ ጉባኤ ማለት በአንድ አገር ወይም ሥፍራ በመንግስት አካላት ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት የተፈጸመን ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት እንዲያጣራ በሕግ ወይም በመንግስት በጎ ፈቃድ የሚቋቋም ገለልተኛ የሆነ የባለሙያዎች ቡድን ነው። ይህ አጣሪ ጉባኤ ተልዕኮው እና የሚኖረው የሥራ ድርሻ ግልጽ፣ በጊዜ የተወሰነ እና አንድ ወይም ከዛ በላይ ባሉ ክስተቶች ላይ ያተኮረ ነው። አጣሪው ጉባኤ ገለልተኛ ፣ ነፃ እና ብቁ መሆን ይኖርበታል። አባላቱም የሰብአዊ መብት ጥሰት ማጣራት ስራውን በበቂ ሁኔታ እንድወጡ የሚያሥችል የሙያ ክህሎት (expertise) እና ብቃት (competence) ሊኖራቸው ይገባል።

በተጨማሪም ይህ አጣሪ ጉባኤ ከሰብአዊ መብት ጥሰት ፈፃሚዎቹም ሆነ ፤ በምርመራው ውጤት ላይ ጥቅም ወይም ፍላጎት (interest) ካላቸው ተቋማት እና ግለሰቦች ገለልተኛ መሆን አለበት። ስለሆነም ገለልተኛ የሰብአዊ መብት አጣሪ ጉባኤ የምንላቸው ነፃ እና ገለልተኛ በሆነ መርህ ላይ ተመሥርተው በአንድ አገር ወይም አካባቢ የተፈፀሙ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ዙሪያ ያሉትን እውነታዎች (facts) ለማጣራት እና በጉዳዩ በቂ የሆኑ ማስረጃዎችን አሰባስበው የተሟላ መግለጫ እንዲያቀርቡ የሚቋቋሙትን አካላት ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ገለልተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች አጣሪ ጉባኤ አይነቶችን በቀጣይ ርዕስ በዝርዝር የምናያቸው ይሆናል።

ገለልተኛ አጣሪ ጉባኤ በበርካታ ሀገሮች የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እንድሁም በአንዳንድ ሃገራት ደግሞ ከፍተኛ የሚባሉ የሙስና እና ሌሎች ሰፋ ያሉ ወንጀሎችን ለማጣራት በሚያስችል መልኩ ተቋቁመው ሲሰሩ ይስተዋላል። ለምሳሌ ደቡብ አፍሪካን የተመለከትን እንደሆነ እ.ኤ.አ ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ የተለያዩ ተልዕኮዎች የተሰጣቸው ከ20 በላይ የሚደርሱ አጣሪ ጉባኤዎች በማቋቋም ትታወቃለች። በአፖርታይድ ጊዜ የተፈፀሙትን ወንጀሎች እና የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን የሚያጣራው የመጀመሪያው ሲሆን በ2018 በፕሬዜዳንት ራምፖዛ የተቋቋመው በአይነቱ ለየት ያለው PIC Commission በሚል በደቡብ አፍሪካ የህዝብ ኢንቨሥትመንት ኮርፖሬሽን ውስጥ የተከሰቱ ብልሹ አሰራሮችን ለማጣራት የተቋቋመው ደግሞ የመጨረሻው ነው።(4)

ከዚህ የምንረዳው በኢትዮጵያ ሌሎች ጉዳዮችንም በተመለከተ ለምሳሌ የተከሰቱ የሙሥና ጉዳዩችን ወይም የአሰቃቂ ተግባር ተዋናዮችን እና ተጎጅዎችን ጉዳይ የሚያጣራ ገለልተኛ ተቋም ማቋቋም እንደሚቻል ነው። ይሁን እንጅ ደቡብ አፍሪካ ይህን ያህል አጣሪ ጉባኤዎችን ብታቋቁምም የጉባኤዎቹን የማጣራት ውጤት መነሻ በማድረግ ተጎጅዎችን የመካስ እና አጥፊዎችን በህግ እንዲቀጡ በመንግስት በኩል መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች አጥጋቢ አለመሆናቸው ሪፖርቶች ይጠቁማሉ።(5) ለዚህም እንደ ዋነኛ ምክንያት ሆኖ የሚጠቀሰው

3.Philip Alston (n 2) 84.

4. The Daily Vox Team, 'All South Africa's commissions of inquiry listed' (August 27, 2020) <https://www.thedailyvox.co.za/all-south-africas-commissions-of-inquiry-listed/> accessed February 25, 2021.

5. SABC News,'what role do commissions of inquiry play in prosecutions?' <https://www.youtube.com/watch?v=BrCM_FunYvI&t=61s> accessed March 4, 2021.

በሚቋቋሙት ተቋማት እና መንግስት መካከል ያለው ግንኙነት እና የማጣራት ውጤቶቹን ተፈፃሚ ለማድረግ በመንግስት በኩል ያለው ተነሳሽነትና ብቃት እጅግ አነስተኛ መሆኑ ነው።

ከደቡብ አፍሪካ ተሞክሮ የምንረዳው ነገር ገለልተኛ የሆነ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን የሚያጣራ ተቋም ወይም ጉባዔ ማቋቋም ብቻ በቂ አለመሆኑን ነው። ከጉባዔ መቋቋም ጋር ተያይዞ እነዚህ ገለልተኛ አጣሪዎች በምርመራ ተመርኩዘው ለሚያቀርቡት የውሳኔ ሃሳብ ተፈጻሚነት የመንግስት የፖለቲካ ቁርጠኝነት፣ በአጣሪው አካል ላይ የፖለቲካ ቁርኝት ወይም ተጽዕኖ አለመፍጠር፤ እንዲሁም የጉባኤዎቹን እንደ ፖለቲካ መሳሪያ (Political Tool) ለመጠቀም አለመሞከር የግድ ይላል። ብዙ ጊዜ ገለልተኛ አጣሪ ጉባኤዎች የሚቋቋሙት በአለም አቀፍ ማህበረሰቡ እና በሰብአዊ መብት ድርጅቶች ጉትጎታ ስለሆነ አንዳንዴ መንግስታት ከሚደርስባቸው ጫና እና አለም አቀፍ ግፊት ለመገላገል ሲሉ ብቻ በተዘዋዋሪ የሚቆጣጠሩት እና ቀጥተኛ ተጽዕኖ የሚያሳርፉበት የመርማሪ ጉባዔ ሊያቋቁሙ ይችላሉ። ለዚህም ነው አጣሪ ጉባኤውን አንዳንድ መንግስታት እንደ ፖለቲካ መሳሪያ ሊጠቀሙበት ይችላሉ የምንለው፤ ይህም ሲባል መነሻ ምክንያቱ መንግስታት ይሄው ገለልተኛ ተቋም መስርተናል በሚል ከተጠያቂነት እና ሃላፊነት ለማምለጥ ተቋሙን እንዳይጠቀሙበት ተገቢ ጥንቃቄ ያስፈልጋል ለማለት ነው።

የገለልተኛ አጣሪ ጉባኤ አይነቶች

የገለልተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት አጣሪ ጉባኤን በሁለት ከፍለን ልናየው እንችላለን። እነዚህም አንደኛ በሀገር ውስጥ በብሄራዊ ደረጃ (National Level) በመንግስት የሚቋቋም ነው። ሁለተኛው አይነት አጣሪ ጉባዔ ደግሞ አለም አቀፍ ይዘት ያለው እና በመንግስት ፈቃድ ሰጪነት ምርመራ የሚያካሂድና እና እውነታውን የሚመረምር አጣሪ ኮሚሽን (International Fact-finding Commission) ነው። ይሁን እንጅ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እውነታ የማጣራት ሂደት በተለያዩ አካላት፣ በተለያየ መንገድ ሊካሄድ ይችላል። ለምሳሌ በተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (UN Human Rights Council) ስር በሚገኙ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ወይም የመብት አይነቶች ላይ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ ልዩ ራፖርተሮች፣ በተ.መ.ድ ቻርተር የተቋቋሙ አካላትም በየተዋቀሩበት ዘርፍ የሚፈጸሙ የመብት ጥሰቶችን በመከታተል ምርመራ ሊያደርጉ እና ለጉባኤው ሪፖርታቸውን ሊያቀርቡ ይችላሉ። እነዚህ አካላት አቤቱታ የሚቀበሉበት፣ ምርመራ የሚያካሂዱበት እና ሪፖርት የሚያቀርቡበት የራሳቸው የአሰራር ስልት እና ደረጃ ስላላቸው የሚያካሂዱት የምርመራ ሂደት ልክ እንደ ሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እውነታ ማጣራት ሂደት ሊጠቀስ ይችላል። እንደየ ሁኔታው የአለም አቀፍ አጣሪ ኮሚሽን በብሄራዊ ደረጃ ያሉትን ተክቶ (in place of) ወይም እንደ ማሟያ (as a complement) ሊቋቋም የሚችልበት ሁኔታም አለ።

እነዚህ የአለም አቀፍ አጣሪ ኮሚሽን የምንላቸው በተለያዩ አለም አቀፍ ወይም አህጉራዊ ተቋማት (Inter-governmental bodies) የሚቋቋሙ ሲሆን በተ.መ.ድ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ህብረት፤ በአውሮፓ ህብረት እንዲሁም በመሳሰሉት ተቋማት ሊቋቋሙ ይችላሉ። ከእነዚህ በተጨማሪ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በተ.መ.ድ የሰብአዊ መብቶች ስምምነት አካላት (UN Human Rights Treaty Bodies) ስር የተለያዩ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እውነታ የሚያጣሩ ስነ ስርአቶች እየተዘረጉ ይገኛሉ። በአሁኑ ጊዜ በአለም ላይ እንደነዚህ ያሉ አሰራሮች እንደመርህ እየተተገበሩ የመጡ ሲሆን በእኛም ሀገር በቅርብ ጊዜያት ለተከሰቱት ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እንደአስፈላጊነቱ በሀገር ደረጃም ሆነ አለም አቀፍ ደረጃ ገለልተኛ አጣሪ ጉባኤ እንድቋቋም ማድረግ አስፈላጊ ነው። በዚህ ክፍል ይህንን ካልን በክፍል ሁለት በአገራችን የነበሩ ተሞክሮዎችን እና 'የገለልተኛ አጣሪ ጉባኤ አስፈላጊነት ከየት እስከ የት ላለው የሰብአዊ መብቶች ጥሰት' በሚል የምንመለስ ይሆናል።

በቀጣይ እትም ይቀጥላል.....

Conflict and Sexual Violence: Highlighting the Case of Ethiopia

Mahlet Abreham Tibebu(1)

Conflicts increase pre-existing patterns of discrimination against women, expose them to heightened risks of violations of their human rights. It particularly can result in higher levels of violence against women and girls, including arbitrary killings, torture, and sexual violence.(2) Women and girls are primarily and increasingly targeted by the use of sexual violence, including as a tactic of war. (3) UN Security Council Resolution 1325 affirmed that sexual violence is often part of the strategy in violent conflicts.(4)

Conflicts affect both women and men in different manners. The majority of the combatants are men who can suffer from direct violence including killings and physical injuries. On the other hand, women suffer disproportionately by the consequence of conflict. They are disproportionately targeted in conflict, which resulted in higher levels of sexual and gender-based violence due to breakdown of law and order, lack of family and community support systems, overcrowded living conditions in refugee/displacement camps and lack of security play a role in such situations.(5) Particularly, rape including gang rape is common sexual violence against women and girls which is used to dehumanize and dishonor the victim, her family, and the community.(6) When ethnicity is a factor in the conflict, women's vulnerability is defined by the intersection of gender with other identities such as class, social status, ethnicity, religion, and sexuality, among others.

Furthermore, when ethnicity or religion is a factor in a conflict, women's vulnerability to sexual and gender-based violence will be double because they will be targeted as women who belong to specific ethnic groups/religion and sometimes from minorities. As Sophia argues, there is a complex intersection of race, sex, ethnicity, class, and sexuality in women's lives including during conflict.(7)

1. The author has LLM in International Human Rights Laws from University of Sussex, LLB in Laws from Haramaya University. Currently working at Ethiopian Human Rights Defenders Center as Program Officer and Gender Consultant at Catholic Relief Service.
2. ' Women's human rights and gender-related concerns in situations of conflict and instability' <https://www.ohchr.org/en/Issues/Women/WRGS/Pages/PeaceAndSecurity.aspx> accessed March 25, 2021.
3. Report of the Special Rapporteur on Violence against Women, Its Causes and Consequences, Radhika Coomaraswamy, submitted in accordance with Commission on Human Rights resolution 2001/49, E/CN.4/2002/83, 31 Jan. 2002, para 122.
4. UN Security Council, Security Council resolution 1325 (2000) [on women and peace and security], 31 October 2000, S/RES/1325 (2000), Para 10.
5. Mireille Le-Ngoc, 'Normative frameworks' role in addressing gender-based violence in disaster settings' (2015) Disaster Law Working Paper Series Paper No. 3, 7.
6. Rashida Manjoo and et al, 'Gender-Based Violence and Justice in Conflict and Post-Conflict Areas', (2011) 44 Cornell Int'l L.J. 11, 14.
7. Sophia Papastavrou, 'Refugee Women, Violence, and War A Return to Transnational Feminist Praxis' (2010) 4 Minerva Journal of Women and War 6, 15.

"IT'S ALWAYS VULNERABLE GROUPS, SUCH AS WOMEN AND CHILDREN PAY THE PRICES DURING SUCH EMERGENCY CRISES. "

She further argues that GBV, specifically sexual violence, is often either dismissed or disregarded as part of the impact of conflict during a conflict. (8) Therefore, there is a need to understand women's experience in a conflict in a way to accommodate their identities. As Mohanty said the experience of violence by all women is not universal or homogeneous; thus, these notions of women's homogeneous characteristics needed to be restructured along the lines of the way violence is understood among diverse women's groups.(9)

Looking at legal framework, CEDAW Committee General Recommendation No 35 on gender-based violence against women, updating general recommendation No. 19 affirm that GBV may affect some women to different degrees due to their varying experience and intersecting forms of discrimination based on women's ethnicity/race, indigenous or minority status, colour, socio-economic status, seeking asylum, being a refugee, internally displaced or stateless.(10) And it recommends to states to enact appropriate laws and policies by taking into account women experience.(11)

8. Ibid.
9.Chandra Talpade Mohanty, Feminism Without Borders: Decolonizing Theory, Practicing Solidarity. Durham, NC: Duke University Press, 2003 46.
10.UN Committee on the Elimination of Discrimination against Women, CEDAW General Recommendation No. 35 on Gender-Based Violence Against Women, Updating General Recommendation No. 19, CEDAW/C/GC/35, Para 12.
11. Ibid.

Conflict is not a recent experience in Ethiopia. It has been caused by a dispute on the possession or use of land grazing land or water resources and access to state resources and question to self-administration.(12) Conflict is not a recent experience in Ethiopia. It has been caused by a dispute on the possession or use of land grazing land or water resources and access to state resources and question to self-administration. (13)

And the recent conflict in Metekel Zones(Benishangul-Gumuz Region)(14) occurred waves of violence against "outsider" communities by heavily armed men. Reports revealed that during these ethnic conflicts hundreds of lives taken inhumanly way and left more than 1 million people displaced.(15) In addition to this, women encounter numerous protection concerns ranging from general protection issues to specific violations related to gender. Atrocities were committed, and sexual violence was used as a weapon of war, and some of them have experienced inter-ethnic gang rapes.(16)

12. Biruk Shewadeg, 'Ethnic Conflict under Ethnic Federalism A Critical Appraisal' The African Centre for the Constructive Resolution of Disputes (ACCORD) March 2019 <https://www.accord.org.za/conflict-trends/ethnic-conflict-under-ethnic-federalism/ > accessed April 13, 2021.
13. Ibid.
14.United Nations Office for the Coordination of Humanitarian Affairs situation Report on Metekel Zone, 29 JAN 2021, <https://www.humanitarianresponse.info/en/operations/ethiopia/document/ethiopia-flash-update-metekel-zone-29-jan-2021-en> accessed March 26, 2021.
15.Maria Gerth-Niculescu, "Anger, fear run deep after months of ethnic violence in western Ethiopia" The New Humanitarian, 23 February 2021, <https://www.thenewhumanitarian.org/news-feature/2021/2/23/fear-runs-deep-after-ethnic-violence-in-western-Ethiopia> accessed on March 26, 2021.
16 A Submission by Civil Society Coalition to the 3rd Universal Periodic Review of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, 'State of vulnerability of internally displaced people and children in Ethiopia' September 2018, See also, Nicola Jones and et al, 'Raising the visibility of IDPs: a case study of gender- and age-specific vulnerabilities among Ethiopian IDP adolescents', The Humanitarian Practice Network (HPN) May 2019<https://odihpn.org/magazine/raising-visibility-idps-case-study-gender-age-specific-vulnerabilities-among-ethiopian-idp-adolescents/> accessed on March 27,2021.

Besides, the recent conflict in Tigray region which was claimed to be a “law enforcement operation” by the Federal government has caused loss of lives, bodily and mental injury, instances of gender-based violence, looting and other human rights violation.(17) Reports revealed that individuals allegedly were forced to rape members of their own family, under threats of imminent violence.(18) Moreover, access to essential services such as health care, including sexual and reproductive health services has disrupted in Tigray region with women and girls being at a greater risk of unplanned pregnancy, maternal mortality and morbidity, severe sexual and reproductive injuries and contracting sexually transmitted infections, including as a result of conflict-related sexual violence.(19)

Conflict has a gender-specific outcome that impacts women and girls differently and disproportionately. Moreover, ethnic conflicts that happened in Ethiopia have increased the vulnerability of women to sexual and gender-based violence. It’s always vulnerable groups, such as women and children who pay the prices during such emergency crises. It’s the obligation of all parties participating in a conflict to respect their duty to protect women from such violence and to commit to a zero-tolerance policy for crimes of sexual violence. Priority should be given to prevent further violence and after committed, the government must investigate and prosecute perpetrators according to International Human Rights and Humanitarian Law.

17. Ethiopian Human Rights Commission brief monitoring report ‘Current Situation of Residents in Tigray Region, February 11, 2021.
18. Ibid.
19. United Nations Special Representative of the Secretary-General on Sexual Violence in Conflict, Prohibition of the use of sexual violence and cease hostilities in the Tigray region of Ethiopia, Press Statement, New York, 21 January 2021.

የንፁሃን ጥበቃ በጦርነት ወቅት

ማህሌት ንጉሴ(1)

"አንድ ሀገር የአለም አቀፍ ህጎችን ስትቀበል የተቀበለችው ህግ ወይም አባል የሆነችበት ስምምነት ልክ እንደ ሀገሪቱ ህግ አካል በመሆን ተፈጻሚነት ይኖረዋል። ሀገሪቱ ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ዜጋ ከዛ የህግ ማዕቀፍ ከሚመጡ መብቶች የመጠቀም እንድሁም ግዴታዎችንም የመወጣት ሀላፊነት አለበት።"

1.መቅድም

በኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ የሚታየው ከፍተኛ የሰላምና መረጋጋት መደፍረስ እየበዛና በሁሉም የሃገራችን ክፍሎች እየተስፋፋ ይገኛል። በተለይም በትግራይ ክልል የተከሰተው ግጭት እና ጦርነት በዋነኛነት ይጠቀሳል። በጦርነቱ የንጹሃን ዜጎች ህይወት መጥፋትን ጨምሮ ከፍተኛ የንብረት ውድመት በተጨማሪ በኢኮኖሚውም ላይ ያሳደረውን ጫና በግልጽ እየታየ ይገኛል። ይህ ጦርነት አሁን ካመጣው አስከፊ ጉዳት አልፎ እንዳይዘልቅ የመታገል ሀላፊነት የመንግስት ብቻ ሳይሆን የሲቪል ማህበራትም ድርሻ ነው።

የጦርነትን አስከፊ ተያያዥ ጉዳቶች ለመቀነስ በአለም አቀፍ ደረጃ የተደነገጉ የህግ ማእቀፎች ማለትም የሰብአዊ መብት ህግ ፣ የሰብዓዊነት ህግ እንዲሁም የሀገር ውስጥ ህጎች ተጠቃሽ ናቸው። በዚህ ፅሁፍ እነዚህን ህጎች እና ሌሎች ጽሁፎችን በማመሳከር ንፁሀን በጦርነት ወቅት ያላቸውን ጥበቃ በዝርዝር እናያለን።

2.መግቢያ

ኢትዮጵያን በመሠሉ ታዳጊ ሀገራት የጦርነት ጉዳት ግልጽና የዜጎችን የመኖር ህልውና ጥያቄ ውስጥ ከማስገባቱ በተጨማሪ የሚያደርሰው የኢኮኖሚ ድቀት ቀላል አይደለም።

በጦርነት ወቅት በህዝቦች ላይ የሚፈጠረውን ችግር ለመቀነስ በአለም አቀፍ ደረጃ ብዙ ስራዎች ተሰርተዋል። በተለይም የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት የህግ ድንጋጌዎች እንዲሁም የሰብአዊነት ህጎች ዋነኞቹ ናቸው። ለአብነት ያህል ሄግ ኮንቬንሽን 1899 እና 1907(እ.አ.አ) ተዋጊ አካላት በጦርነት ወቅት ማድረግ ያለባቸውን ግዴታዎች ሲደነግግ በሌላ በኩል ደግሞ ጄኔቫ ኮንቬንሽኖች ስለንጹሃን ዜጎች ጥበቃ ያትታሉ።

ጦርነትን ወይም ግጭትን በሁለት መንገድ ከፍለን ልናየው እንችላለን። የመጀመርያው አለም አቀፋዊ የትጥቅ ትግል (international armed conflict) ሲባል ይህ አይነቱ ጦርነት በሁለት ሉአላዊ ሀገራት መካከል የሚደረግ ጦርነት ነው። ሁለተኛው አይነት ጦርነት አለም አቀፋዊ ያልሆነ ሀገራዊ ወይም ውስጣዊ (non-international armed conflict) ሲባል ይህ አይነቱ ጦርነት በአንድ ሉአላዊ ሀገር እና በሌላ የተደራጀ ቡድን ወይም በሁለት የተደራጁ ቡድኖች መካከል የሚደረግ ጦርነት ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ በሁለት ተዋጊ አካላት መካከል ግጭት ሲኖር እና ሌላ ሉአላዊ ሀገር አንዱን አካል ለመርዳት በጦርነቱ ላይ በምትሳተፍበት ጊዜ ጦርነቱ መጀመሪያ የያዘዉን ስያሜ ማለትም ሀገራዊ ወይም ውስጣዊ ጦርነትነቱን ይለቅና አለም አቀፋዊ (internationalized armed conflict) ይሆናል።

1. ጸሀፊዋ ከባህር ዳር ዮኒቨርስቲ በ2012/ 2013 ዓ.ም በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ አላት።

ከላይ የተገለጹትን አይነት ጦርነቶች አስከፊ ውጤት ለመቀነስ ሲባል በልዩ ሁኔታ የተቀረጸ ህግ አለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ይባላል። ይህ ህግ በጦርነት ላይ ተሳትፎ የሌላቸውን ሰዎች ለመጠበቅ ሲባል ከጦር መሳርያ አጠቃቀም ጀምሮ በግጭቱ ላይ ተሳትፎ ያላቸውን ሰዎች በግልጽ በመለየት ለንጹሃን ጥበቃ ይሰጣል። የሰብአዊነት ህግ ተግባራዊ የሚሆነው በጦርነት ወቅት ብቻ ሲሆን የሚዳኘው የጦርነትን አስፈላጊነት ወይም አግባብነት ሳይሆን የንጹሃን ዜጎችን ጥበቃ ነው። ይህ የህግ ማዕቀፍ ለንፁህን ዜጎች እና ትኩረት ለሚሹ ሰዎች ዐብይ መርሆችን ያስቀመጠ ሲሆን ንጹሃን ዜጎችን የመለየት መርህ፤ በጦር ምርኮኞች ወይም ተጎጂዎች ላይ ጥቃት ያለማደረስ መርህ፤ አላስፈላጊ የሆነ ስቃይን የሚያደርስ ጥቃት ያለመሰንዘር መርህ፤ የተመጣጠነ ጥቃት የማድረስ መርህ እንዲሁም የሰብአዊነት መርህ ዋነኞቹ ናቸው።

3.ተዋጊ አካላት (combatant)

የጄኔቫ ኮንቬንሽን አዲሽናል ፕሮቶኮል 1 አንቀጽ 48 እና 52 ፣ የ1899 እና 1907 (እ.አ.አ) ሄግ ሬጉሌሽን አንቀጽ 3 ተዋጊ ወገኖች ማን እንደሆኑ እና በምን እንደሚለዩ በዝርዝር ያስቀምጣሉ። በተለይም የጄኔቫ ኮንቬንሽን 3 እንዲሁም የሄግ ሬጉሌሽን አንቀጽ 1 የአንድ ሀገር መንግስት የጦር አባላት፤ ሚሊሻ እንዲሁም በበጎ ፈቃደኝነት በጦርነት ላይ የተሳተፉ፤ በበላይ አካል ወይም አመራር የሚታዘዙና በግልጽ የጦር መሳርያ ይዘው የሚንቀሳቀሱ ሰዎችን ተዋጊ ብሎ ይሰይማቸዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የአንድ ሀገር የጦር አባላት ምንም እንኳን የወታደራዊ ህጉን ጥሰው ወይም ጥፋት አጥፍተው ቢገኙ በጦር ወንጀል ይቀጡ ይሆናል እንጂ ተዋጊ የሚል ስያሜያቸውን ሊያጡ አይችሉም።

4.ንጹሃን ዜጎች (civilians)

በአዲሽናል ፕሮቶኮል 1 አንቀጽ 50 መሰረት ንጹሀን ዜጎች የምንላቸው በጦርነት ወይም በግጭት ወቅት ቀጥተኛ የሆነ ተሳታፊነት የሌላቸው እንዲሁም በየትኛውም መንገድ ቢሆን በጦርነት ከሚመጣ አላግባብ ስቃይ እና ጉዳት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሊጠበቁ የሚገባቸውን ሰዎች ነው። በዚህ ረገድ በዋናነት ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማለት ምን ማለት ነው የሚለው ነው።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ለኤልሳቫዶር ልዩ ተወካይ ኮሚሽን ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲሁም ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳትፎ ምን እንደሆነ ይገልጻል። ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳትፎ የምንላቸው በጥቂቱ ለአንዱ ወይም ለሁለቱም ወገኖች ቁሶችን መሸጥ፣ ሀዘኔታ ወይም ድጋፍን መግለጽ፣ መንገዶችን መጠገን እና ሌሎችም እነደ ሁኔታው የሚታዩ ሲሆኑ ቀጥተኛ ተሳትፎ እና ጥበቃን የሚያሳጡ የምንላቸው ደግሞ በአዲሽናል ፕሮቶኮል 1 አንቀጽ 51 እንዲሁም አዲሽናል ፕሮቶኮል 2 አንቀጽ 13 ላይ የተዘረዘሩት ናቸው። በዚህም መሰረት ሰዎችን የሚገሉ፣ የሚያግቱ፣ የጦር መሳርያ የሚያወድሙ፣ የሚሰልሉ፣ ምሽጎችን የሚጠቁሙ እንዲሁም በጦርነት ላይ ለመሳተፍ በዝግጅት ላይ ያሉ ዜጎች እንደ ተዋጊ ተቆጥረው ተገቢው እርምጃ ሊወሰድባቸው ይችላል። ይህ ሲሆን ግን አሳማኝ በሆነ ማስረጃ መረጋገጥ ይኖርበታል። ከላይ ከተጠቀሱት ሰዎች በተጨማሪ እንደ ንጹኃን ዜጎች ሊቆጠሩ የሚችሉት ጋዜጠኞች ናቸው። በአዲሽናል ፕሮቶኮል 1 አንቀጽ 79 መሰረት በአስቸጋሪ የጦርነት ወቅት በጦር ሜዳ ተገኝተው መረጃን ለህዝብ የሚያደርሱ ጋዜጠኞች እንደ ንጹኃን ዜጎች ይቆጠራሉ። ይህም ማለት እንደ አንድ በጦርነት ላይ ተሳትፎ እንደሌለው ሰው ይቆጠራሉ እንጂ የተለየ ጥበቃ ይደረግላቸዋል ማለት አይደለም። መብታቸው እንዲከበር ሌላ የጎንዮሽ ተልእኮ ሊኖራቸው አይገባም ይህ ሆኖ ቢገኝ ግን እንደንፁህ የመቆጠር ጥበቃቸውን ሊያጡ ይችላሉ።

5. የንጹሃን ዜጎች ጥበቃ በጦርነት ወቅት

በጦርነት ወቅት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ኢላማ ወይም ተጠቂ የሚሆኑት ተዋጊዎች ሲሆኑ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ጥበቃ የሚደረግላቸው ደግሞ ንጹሃን ዜጎች ናቸው። ነገር ግን በተቃራኒው ንጹሃን ዜጎች በጦርነት ወቅት ለተለያዩ ጥቃቶች በተለይም ለዘር ማጥፋት፤ ለዘር ማጽዳት፤ ለመፈናቀል፤ ለረሀብ እንዲሁም ለጾታዊ ጥቃቶች ሰፋ ባለ መልኩ ተጋላጭ ይሆናሉ።

በአዲሽናል ፕሮቶኮል 1 አንቀጽ 48 እና 52 መሰረት ተዋጊ አካላት እነ ማን ተዋጊ እነ ማን ንጹሃን እንዲሁም የትኞቹ ቁሳቁሶች የጦር ኢላማ የትኞቹ የንጹሃን ንብረቶች እንደሆኑ የመለየት ግዴታ አለባቸው።

ማንኛውንም ጥቃት በንጹሃን ዜጎች እንዲሁም በንብረታቸው ላይ ማድረስ አለም አቀፍ ህጎችን መጣስ ብቻ ሳይሆን እንደ ጦር ወንጀል እና በሰብዕና ላይ እንደሚፈጸሙ ወንጀሎች ሊቆጠር የሚችል ከባድ ጥሰት ነው።(2) በንጹሃን ዜጎች እና በተዋጊዎች መካከል ልዩነት ሊፈጥር የማይችል ማንኛውም አይነት መሳርያ በጦርነት ላይ መጠቀም ፍጹም የተከለከለ ሲሆን ይህም እንደ ዓለም አቀፋዊ የባህል ህግ (International customary law) ተቀባይነት ያለው እና ሁሉን ገዝ ነው። ይህ የንጹሃን ዜጎች ጥበቃ በአዲሽናል ፕሮቶኮል 1 አንቀጽ 48፤ 51 እንዲሁም አንቀጽ 85 እና በአዲሽናል ፕሮቶኮል 2 አንቀጽ 13 የተገለጸ ሲሆን የንጹሃን ዜጎች ንብረት ጥበቃም በተመሳሳይ በአዲሽናል ፕሮቶኮል 1 አንቀጽ 56 እና 85 ላይ ተቀምጧል። ማንኛውም ተዋጊ ሙሉ ለሙሉ እርግጠኛ ባልሆነበት ሁኔታ በንጹሃን ዜጎች ላይ ጥቃት መሰንዘር አይችልም። በተጨማሪም የጄኔቫ ኮንቬንሽን 3 ፤ አለም አቀፍ የቀይ መስቀል እና የቀይ ጨረቃ ማእከሎች በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ ንጹሃን ዜጎችን እንደ ከለላ በመጠቀም ጥቃት መፈጸም እንደማይቻል በግልጽ ያስረዳሉ። ተዋጊ ወገኖች ራሳቸውን ከንጹሃን ዜጎች በማያወላዳ መልኩ የመለየት ግዴታ አለባቸው። ንጹሃን ዜጎችን በጦር አመራር ላይ እንደ ማሸነፍያ መንገድ ወይም እንደ ከለላ መጠቀም ፈጽሞ የተከለከለ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ በሄግ ኮንቬንሽን ከአንቀጽ 25 እስከ 28 ላይ እንደተገለጸው ንጹሃን ዜጎች ሰፍረው የሚኖሩባችው መንደሮች እና ከተሞች ለጥቃት ሰለባ ሊሆኑ አይገባም። የጦር መሪዎች የጦር መሳሪያን ከመጠቀማቸው በፊት ንጹሃን ዜጎችን ከቦንብ እና መሰል ፍንዳታዎች የመጠበቅ ስትራቴጂ ሊቀርጹ ይገባል ይህም በሄግ ኮንቬሽን አንቀጽ 26 ላይ ተቀምጧል። በተጨማሪም ተዋጊ ወገኖች በጦርነት ጊዜ ለሀይማኖት ተቋማት፤ ለኪነጥበብ ተቋማት፤ ለስነጥበብ መዘክር ተቋማት፤ ለታሪካዊ ቅርሶች፤ ለጤና ተቋማት እንዲሁም ለትምህርት ቤቶች ልዩ ትኩረት የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

ከላይ ከተጠቀሱት ማንኛውም ሰው በጦር ህጎች ከተከለከሉ የጦር ስልቶች እንዲሁም መሳርያዎች የመጠበቅ መብት አለው።

"ማንኛውም ሰው" የሚለውን ቃል የተጠቀምንበት ምክንያት ይህ ጥበቃ ለንጹሃን ብቻ የተሰጠ ጥበቃ ባለመሆኑ ነው። ተዋጊዎች ልክ እንደ ንጹሃን አላስፈላጊ ከሆነ ስቃይ የመጠበቅ መብት አላቸው። በሌላ መልኩ አንዱ ለንጹሃን መጠበቂያ ወሳኙ መርህ የተመጣጣኝነት መርህ ነው። ይህ መርህ በወታደራዊ ጠቀሜታ እና በንጹሃን ጥበቃ መካከል ያለውን ልዩነት ይዳኛል። በዚህም መሰረት የንጹሃን ጉዳት ወይም ጥቃት በምንም መልኩ ከወታደራዊ ጠቀሜታ የበለጠ ዋጋ ሊሰጠው አይገባም። ይህም በ 'አዲሽናል ፕሮቶኮል' 1 አንቀጽ 51(5) ላይ ተገልጿል። የተመጣጣኝነት መርህ ተፈጻሚ ሆነ የሚባለው ተዋጊ ወገኖች የሰብዓዊ ህግን አክብረው በተመሳሳይ የወታደራዊ ጠቀሜታን ማስፈጸም ሲችሉ ነው።

5.1 ልዩ ጥበቃ የሚሹ ሰዎች (ንጹሃን)

ልዩ ጥበቃ የሚሹ ንፁሃን የሚባሉት በጦርነት ወቅት የተለየ ተጋላጭነት ያላቸው ሰዎች ማለትም ሴቶች፤ ህፃናት፤ ስደተኞች እና አረጋዊያን ናቸው። አዲሽናል ፕሮቶኮል 1 አንቀጽ 51 ፤ አዲሽናል ፕሮቶኮል 2 አንቀጽ 17 እንዲሁም ካምፓላ ኮንቬንሽን ለስደተኞችና ከመኖርያ አካባቢያቸው ለተፈናቀሉ ሰዎች ጥበቃ ይሰጣል። ይህ ጥበቃ ከጥቃት ከመታደግ በዘለለ የሰብዓዊ እርዳታ ተጠቃሚ መሆንንም ይጨምራል። ስደተኞች የአንድ ሀገር ዜጋ ያለውን አይነት ተመሳሳይ ጥበቃ በሰብዓዊነት ህግ መሰረት ያገኛሉ። የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር መጋቢት 2001(እ.አ.አ) ባደረገው ስብሰባ ላይ የስደተኞች ካምፕ ጥቃት ሊሰነዘርበት እንደማይገባ እና ከጦር ሜዳ መለየት እንዳለበት ተገልጻል። ህጻናት ከሌሎች ልዩ ጥበቃ ካላቸው ሰዎች የሚለዩት ምንም እንኳን በጦርነት ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ ያላቸው ቢሆንም እንኳን ልዩ ጥበቃቸውን ሊያጡ ስለማይችሉ ነው። የ1989 (እ.አ.አ) የህጻናት መብት ኮንቬንሽን አዲሽናል ፕሮቶኮል እና የኮንቬንሽኑ ኦብሽናል ፕሮቶኮል ህጸናትን በጦርነት ማሳተፍን ይከለክላል። በአዲሽናል ፕሮቶኮሉ መሰረት ከ15 አመት በኦብሽናል ፕሮቶኮሉ መሰረት ደግሞ ከ18 አመት በታች የሆኑ

2. Antonio cassese et al, Casseses international criminal law, (3rd edn), Oxford university press www.oxfordtextbook.co.uk/orc/casseseicl3e/

ህጸናትን በጦርነት ላይ ማሳተፍ የተከለከለ ነው።ይህ ክልከላ እንዳለ ሆኖ እድሜያቸው ከላይ ከተጠቀሰው በታች የሆኑ ህጸናት በጦርነት ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ ኖሯቸው ቢገኝ እንኳን እንደ ተዋጊ ተቆጥረው የጦር እስረኛ ይሆናሉ እንጂ ሊሰጣቸው የሚገባውን ልዩ ጥበቃ አያሳጣቸውም። ይህም በጄኔቫ ኮንቬንሽን 3 አንቀጽ 77 እንዲሁም አዲሽናል ፕሮቶኮል 2 አንቀጽ 4 ላይ ተገልጿል። ከዚህ በዘለለ በጄኔቫ ኮንቬንሽን 4 ፣ በአዲሽናል ፕሮቶኮል 1 እንዲሁም በአዲሽናል ፕሮቶኮል 2 መሰረት ህጻናት ከጦር ሜዳ የመራቅ ሰላም እና መረጋጋት የሰፈነበት ቦታ የመኖር ፣ የእንክብካቤ እና ድጋፍ ፣ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ከተነጠሉ የመገናኘት እንዲሁም ከሞት ፍርድ ነጻ የመሆን መብት አላቸው።

በተጨማሪም ሴቶች ልዩ ጥበቃ የማግኘት መብት አላቸው። ሴቶች እንደ ተዋጊም እንደ ንጹህ ዜጋም ጥበቃ ሊደረግላቸው ይችላል። ተዋጊ ሆነው ጥበቃ ተደረገላቸው የሚባለው በጠላት እጅ ከገቡ ወይም የጦር እስረኛ ከሆኑ በኃላ ሴት ታራሚዎች ወደሚገኙበት የሴቶች ማረሚያ ሲወሰዱና ለሴትነታቸው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ሲቀርቡላቸው ነው። ሴት ታራሚዎችን ከወንድ ታራሚዎች ጋር ማሰር አጥብቆ የተከለከለ ሲሆን እንደ ንጹህ ዜጋ ልዩ ጥበቃ ተደረገላቸው የሚባለው ደግሞ ከጦር ሜዳ ከማራቅ ጀምሮ በተለይም ለእርጉዝ፣ ህጻናት ልጆች ላሏት እናት የተለየ እንክብካቤ ሲደረግ ነው። ይህም ምግብን፣ የጤና ጥበቃን እንዲሁም አልባሳትን ሊጨምር ይችላል። በዋናነት ግን ሴቶች ከጾታዊ ጥቃት ከጠለፋ፣ ከወሲብ ባርነት እንዲሁም ከህገወጥ የሴቶች ዝውውር መጠበቅ እንዳለባቸው በጄኔቫ ኮንቬንሽን 4 በግልጽ ተቀምጧል።

6. የሰብዓዊነት ህግ በኢትዮጵያ

አንድ ሀገር የአለም አቀፍ ህጎችን ስትቀበል የተቀበለችው ህግ ወይም አባል የሆነችበት ስምምነት ልክ እንደ ሀገሪቱ ህግ አካል በመሆን ተፈጻሚነት ይኖረዋል። ሀገሪቱ ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ዜጋ ከዛ የህግ ማዕቀፍ ከሚመጡ መብቶች የመጠቀም እንድሁም ግዴታዎችንም የመወጣት ሀላፊነት አለበት። በሌላ ቋንቋ አንድ አካል ከአንድ ሀገር አፈንጋጭ ወይም አማፂ ቢሆንና ይህችን ሀገር ለመውጋት ቢነሳ የዛ ሀገር ዜጋ እስከሆነ ድረስ ሀገሪቱ አባል ለሆነችባቸው አለም አቀፋዊ የህግ ማዕቀፎች ሁሉ ተገዢ ነው ማለት ነው።

ይህም በጦርነት ወቅት የሰብአዊነት ህግን እንዲያከብር ካላከበረም በጦር ወንጀል እንዲሁም ስብእና ላይ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች ተጠያቂ እንዲሆን ያደርገዋል። የሰብአዊነት ህግ በሁለት ተዋጊ ወገኖች ላይ እኩል ግዴታ ይጥላል።

ኢትዮጵያ የተለያዩ አለም አቀፍ ኮንቬንሽኖች አባል ናት። ለአብነት ያህል አራቱ የጄኔቫ ኮንቬንሽኖችን እንዲሁም ሁለቱን አዲሽናል ፕሮቶኮሎች ተቀብላለች።(3) የኢፌድሪ ህገመንግስት አንቀጽ 9 እንደሚደነግገው ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው አለም አቀፍ ህጎች ልክ እንደ ሀገሪቱ ህጎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል። በሌላ በኩል የህገመንግስቱ አንቀጽ 28 በሰብዕና ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች በማንሳት ወንጀሉ የይርጋ ጊዜ እንደማያግደው እና በምህረት ወይም በይቅርታ እንደማይታለፍ ያስረዳል፤ ሆኖምበሰብዕና ላይ የሚፈጸም ወንጀል ምን ምን እንደሚያካትት በግልፅ አልተቀመጠም። ኢትዮጵያ አባል በሆችባቸው አለም አቀፍ የህግ ማዕቀፎች መሰረት ይተረጎማል። በተመሳሳይ የህገመንግስቱ አንቀጽ 18 ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ ስለመከልከሉ ያስረዳል ይህም በጦርነት ወቅት ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ በበኩሉ የአለም አቀፍ ህጎችን እንዲሁም ህገመንግስቱን ከግምት ውስጥ በማስገባት ከአንቀጽ 269 ጀምሮ ስለተለያዩ የህግ ጥሰቶች ያስረዳል። በዚህም መሰረት በአንቀጽ 269 ስለ ዘር ማጥፋት ወንጀል፣ በአንቀጽ 270 ስለ ጦር ወንጀል፣ በአንቀጽ 274 ከላይ የተጠቀሱትን ወንጀሎችን ስለማነሳሳት ወይም ዝግጅት ስለማድረግ፣ በአንቀጽ 276 አግባብ ያልሆነ የጦር መሳርያ መጠቀምን እንዲሁም በአንቀጽ 278 ቀጥተኛ ጥቃት በአለም አቀፍ ድርጅቶች ላይ መሰንዘር ወንጀል እንደሆነ በግልጽ ያስረዳል።

በቀጣይ እትም ይቀጥላል.....

3. . ከላይ እንደተመለከተው አራቱ የጄኔቫ ኮንቬንሽኖች እና ሁለቱ አዲሽናል ፕሮቶኮሎች ማለት

- Geneva convention 1 for the amelioration of the condition of the wounded and sick in armed force in the field, Geneva 12 August 1949
- Geneva convention 2 for the amelioration of the condition of the wounded and sick shipwrecked members of the armed forces at sea , Geneva 12 August 1949
- Geneva convention 3 relative to the treatment of prisoners of war , Geneva 12 August 1949
- Geneva convention 4 relative to the protection of civilian persons in time of war, Geneva 12 August 1949
- Protocol additional to the Geneva convention of 12 August 1949, and relating to the protection of victims of international armed conflict , Geneva 8 June 1977
- Protocol additional to the Geneva convention of 12 August 1949, and relating to the protection of victims of non-international armed conflict , Geneva 8 June 1977

ስብስብ ለሰብአዊ መብቶች በኢትዮጵያ መንግስታዊ ያልሆነ፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ ለሰብአዊ መብቶች መከበር በሀገር አቀፍ ደረጃ ሰፋ ያሉ ጥናቶችን በማድረግ በመረጃ የተደገፈ ምርመራ የሚያደርግ እና ለተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ተሟጋች በመሆን በሌሎች የሰብአዊ መብት ድርጅቶች በተለያዩ ምክንያቶች ያልተዳሰሱ የሰብአዊ መብቶችን የማስጠበቅ ተግባራትን የሚያከናውን ተቋም ነው።

ስሰመኢ ከተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጪ ድርጅቶች ጋር በትብብር ለተመሳሳይ አላማ በመስራት ያምናል፤ በመሆኑም ከተለያዩ አለም አቀፍ እና ሀገር በቀል ድርጅቶች ጋር ይሰራል። በተጨማሪም ለተለያዩ የሀገር ውስጥ ሲቪል ማህብራትና ሌሎች ድርጅቶች ሰብአዊ መብቶችን በተመለከተ ስልጠናዎችን በመስጠት ድጋፍ ያደርጋል።

Association for Human Rights in Ethiopia



ስብስብ ለሰብአዊ መብቶች በኢትዮጵያ